# የክፍያዎች እና የአገልግሎት ክፍያዎች ሥርዓት (SOPAF) ለቤተሰቦች የሚሆኑ ግብዓቶች



ይህ ግብዓት ቤተሰቦች SOPAFን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ እና በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲያደርጉ ይረዳል እንዲሁም ይደግፋል።

## SOPAF ምድንድ ነው?

SOPAF ማለት System of Payments and Fees (የክፍያዎች እና የአገልግሎት ክፍያዎች ሥርዓት) ማለት ነው። SOPAF ቤተሰብዎ ለEarly Support for Infants and Toddlers (ለሕፃናት እና ለትናንሽ ልጆች የሚሰጥ ቅድመ ድጋፍ፣ ESIT) አገልግሎቶች ምን ያህል እንደሚከፍል ለመወሰን ያግዛል። እንደ ግምገማዎች ያሉ አንዳንድ አገልግሎቶች ሁል ጊዜ ነፃ ናቸው። ለሌሎች አገልግሎቶች፣ ቤተሰቦች በከፊል ክፍያ እንዲከፍሉ ኃላፊነት ሊኖርባቸው ይችላሉ። የሚከፍሉት የክፍያ መጠን በመድን፣ በቤተሰብ መጠን፣ በገቢ እና ልጅዎ በሚያገኛቸው አገልግሎቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

እርስዎ ላልዎት የመድን ዓይነት የSOPAF ቅጾችን እንዲሞሉ ይጠየቃሉ። አቅራቢዎ መድንዎን እንዲከፍል ለመፍቀድ ለአቅራቢዎ ፈቃድዎን እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። የሒሳብ ክፍያ መድን አቅራቢዎ አገልግሎቱን ለማቅረብ የሚያወጣቸውን የተወሰኑ ወጪዎች እንዲሸፍን ያግዘዋል። ለመድንዎ ያልዎትን መዳረሻ ከከለከሉ፣ ወርሀዊ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ሊኖርብዎት ይችላል።



## የመድኖች ዓይነት

### የሕዝብ

Apple Health ካለዎት፣ መዳረሻን ቢያቆሙም እንኳን አገልግሎቶች ሁልጊዜ ነፃ ይሆናሉ። Child Health Insurance Program (የሕፃን ጤና መድን ፕሮግራም፣ CHIP) ካለዎት፣ ለመድንዎ ያልዎትን መዳረሻ ካቆሙ፣ ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ሊኖርብዎት ይችላል። ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያዎ የሚመሰረተው በቤተሰብዎ መጠን እና በቤተሰብዎ ገቢ ላይ ነው።

### የግል

የግል መድን ወይም TRICARE ካለዎት፣ ቋሚ ክፍያዎችዎን እና ከኢንሹራንስ በፊት የሚከፈሉ የመጀመሪያ ክፍያዎችዎን ለመክፈል ወይም ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያን ለመክፈል መምረጥ ይችላሉ (ከእውነተኛው የአገልግሎቶች ወጪ በላይ በጭራሽ አይሆንም)። የአገልግሎት አስተባባሪዎ የትኛው አማራጭ የተሻለ እንደሆነ ለመወሰን ሊያግዝዎት ይችላል። ለመድንዎ ያልዎትን መዳረሻ ካቆሙ፣ በቤተሰብዎ መጠን እና በቤተሰብዎ ገቢ ላይ በመመስረት ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላሉ።

### የሕዝብ እና የግል

ቤተሰብዎ Apple Health እና የግል መድን ካለው፣ ምንም ዓይነት ቋሚ ክፍያዎችን ወይም ከኢንሹራንስ በፊት የሚከፈሉ የመጀመሪያ ክፍያዎችን አይከፍሉም።

### መድን የሌላቸው ወይም የመድን ዝርዝሮችን የማያቀርቡ ቤተሰቦች

ቤተሰብዎ መድን ከሌለው ወይም እርስዎ የመድን ዝርዝሮችን ካላካፈሉ፣ እንግዲያውስ የቤተሰብዎን መጠን እና የቤተሰብ ገቢን መሠረት በማድረግ ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላሉ። የገቢዎን እና የወጪዎን ዝርዝሮች ማካፈል ካቆሙ፣ በቤተሰብዎ መጠን መሰረት ከፍተኛው የክፍያ እርከን ላይ ይመደባሉ።

Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

## የመክፈል አቅም

ቤተሰብዎ የግል ኢንሹራንስ ወይም TRICARE ካለው፣ «የመክፈል አቅም» ውሳኔ እንዲኖርዎ መምረጥ ይችላሉ። ገቢዎ ከFederal Poverty Limit (የፌዴራል ድህነት ገደብ፣ FPL) ጋር ይነጻጸራል። ገቢዎ ከFPL 200% በታች ከሆነ፣ አገልግሎቶች ነፃ ይሆናሉ። ገቢዎ ከ200% በላይ ከሆነ፣ ቋሚ ክፍያዎችዎን እና ከኢንሹራንስ በፊት የሚከፈሉ የመጀመሪያ ክፍያዎችዎን ለመክፈል ወይም ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያን ለመክፈል መምረጥ ይችላሉ። «የመክፈል አቅም» አማራጭ ሲሆን በማንኛውም ጊዜ ሊጠየቅ ይችላል።

## የገቢ እና የወጪ መረጃ

ቤተሰብዎ ቋሚ ክፍያዎችን እና ከኢንሹራንስ በፊት የሚከፈሉ የመጀመሪያ ክፍያዎችን የሚከፍል ከሆነ፣ የገቢ እና የወጪ ዝርዝሮች አያስፈልጉም። ቤተሰብዎ ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያ የሚከፍል ከሆነ፣ ወይም «የመክፈል አቅም» ሲወሰን ወይም የአቅም ችግር እንዳለ ሲጠየቅ፣ የገቢ እና የወጪ ዝርዝሮች ያስፈልጋሉ።

## የአቅም ችግር ላለባቸው ነፃ የሚደረግ ነገር

ቤተሰብዎ ቋሚ ክፍያዎችዎን፣ ከኢንሹራንስ በፊት የሚከፈሉ የመጀመሪያ ክፍያዎችዎን ወይም ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያዎን መክፈል ካልቻለ፣ በአቅም ችግር ምክኛት ነፃ እንዲደረግልዎት መጠየቅ ይችላሉ። የአገልግሎት አስተባባሪዎ ነፃ እንዲደረግልዎት የጠየቁትን ጥያቄን እንዲያጠናቅቁ ያግዙዎታል፣ እና አቅራቢዎ ጥያቄዎን ይገመግማል። ነጻ መደረጉ ተቀባይነት ካገኘ፣ ቤተሰብዎ አገልግሎቶችን በነፃ ያገኛሉ። ነጻ መደረጉ ከተከለከለ፣ ቋሚ ክፍያዎችዎን፣ ከኢንሹራንስ በፊት የሚከፈሉ የመጀመሪያ ክፍያዎችዎን ወይም ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያዎን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርብዎታል። ነፃ መደረግ በማንኛውም ጊዜ ሊጠየቅ ይችላል እና የ«የመክፈል አቅም» ውሳኔን ይጠይቃል።

## ቅጾች በምን ያህል ጊዜ ይሞላሉ

ሁሉም ቤተሰቦች በየዓመቱ እና አገልግሎቶችን መጠቀም ከመጀመራቸው በፊት የSOPAF ቅጾችን ይሞላሉ። የግል መድን ወይም TRICARE ላላቸው ቤተሰቦች፣ ቤተሰብዎ የሚከፍለው መጠን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ለውጥ በሚኖርበት በማንኛውም ጊዜ ቅጾች ይታደሳሉ።

## የክፍያዎች መዘግየት

ክፍያዎችዎን መፈጸም አስፈላጊ ነው። ቤተሰብዎ መክፈል ካልቻለ፣ እባክዎ «የመክፈል አቅም» ውሳኔን እና አስፈላጊ ከሆነም በአቅም ችግር ምክኛት የክፍያ ነፃ መደረግን ለማጠናቀቅ የአገልግሎት አስተባባሪዎን ያነጋግሩ። ክፍያዎች መከፈል ካለባቸው ቀን 90 ቀናት ሳይከፈሉ ካለፉ፣ አገልግሎቶች ሊቋረጡ ይችላሉ። ያልተከፈለው ቀሪ ሒሳብዎ ለሰብሳቢ ኤጀንሲ ሊላክ ይችላል።

### የበለጠ መረጃ ለማግኘት

የSOPAF ፖሊሲ፣ ቅጾች እና የክፍያ መርሃ ግብር ከአገልግሎት አስተባባሪዎ ሊጠየቁ ይችላሉ። በተጨማሪም በ«ክፍያዎች እና የአገልግሎት ክፍያዎች ሥርዓት ፖሊሲ እና ተዛማጅ ሰነዶች» ስር በESIT ድር ጣቢያ ላይ በ**https://dcyf.wa.gov/services/child-dev-support-providers/esit/forms-publications** ይገኛሉ።

*የዚህን ህትመት ቅጂ በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ በነፃ ማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎ የDCYF የደንበኛ ግንኙነቶችን በ1-800-723-4831 ያነጋግሩ ወይም ወደ* ***communications@dcyf.wa.gov*** *ኢሜይል ያድርጉ።*

DCYF PUBLICATION FS_0091 AM (12-2025) Amharic